# ስልጣን በምርጫ ወይስ በጡንቻ!!

## በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች
## ስብስብ የተሰጠ የጋራ የአቋም መግለጫ

ፍትሓዊ ምርጫ የህዝቡን ስልጣንና መብት ማረጋገጫ መሆኑን የታወቀ ቢሆንም በተለይም በኢትዮጵያ በአተረጓጎሙ፣ በይዘቱና በተግባራዊነቱ ሲያወዛግብና ከዚያም አልፎ ደም ሲያፋስስ ቆይቷል። ህወሓት/ኢሕአዴግ የሚከተለዉ አብዮታዊ ዲሞክራሲ እርሱ በርሱ የተምታታ የመደናገሪያ ስርዓት ነው የምንልበት አንዱም በምርጫ፣ በዲሞክራሲና በብዙሃን ፓርቲ ስርዓት ዙሪያ ያለው የተዛባ አሰራርና ድብቅ አላማ ነው ብለን ስለምናምን ነው። ምርጫ ገዢው ፓርቲ ለውጪ ዓለም በተለይም ለምዕራባውያን ለጋሽ ሀገሮች በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እንዳለ አስመስሎ ለማቅረብ እንደ ድራማ አድርጎ ይጠቀምበታል እንጂ በኢትዮጵያ ከሀገሪትዋ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ምርጫ እንዲኖር የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ባህርይ ፈፅሞ እንደማይፈቅድ ባለፉት ተከታታይ የምርጫ ዙሮች አይተናል። የህዝብ ድምፅ ይከበር ብለዉ ለጮኹ ዜጎች የደረሰባቸው ጭካኔ የተሞላበት ግድያና አፈናም በሃዘን የምናስታውሳቸው ናቸው።

በብዙኃን ፓርቲ ስርዓት ዙሪያ ያለው አካሄድም ተመሳሳይ ነው። እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ተፈጥሯል የተባሉት የፓለቲካ ድርጅቶች በኢሕአዴግ ተለክቶ በሚሰጣቸው መጠንና ርቀት የሚጓዙ እንጂ ከዚያ ውጭ መሄድ አይችሉም። ከዚያ ውጭ ከሄዱ ግን ገዢው ፓርቲ ህልውናዬ ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ አካሄድ ነው ብሎ ስለሚያስብ በሓይል እርምጃ እንዲቆሙ ወይም እንዲጠፉ ይደረጋል። የስርዓቱ አወቃቀርና የዘረጋው መረብም የሌሎቹ ተቃዋሚ ሓይሎች እንቅስቃሴዎች ለመቆጣጠር፣ ለማደከምና ብሎም ለማጥፋት በሚችል መልኩ የተደራጀና የተበተበ ነው። ለዚህ አብነትም የህዝቡን የደሚክራሲና የፍትሕ ጥያቄ ለማዳፈን ሲባል በኢትዮጵያ ኢሕአዴግን ሊወዳደርና ሊተካ የሚችል ትርጉም ያለው ተቀናቃኝና አማራጭ ድርጅት እንዳይፈጠር በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ ክልሎች ለምርጫ በሚንቀሳቀሱ የፓለቲካ ድርጅቶችና አባላቶቻቸው እንዲሁም ብቃት አላቸው ሊያሸንፉ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ ዕጩ ተመራጮችና መራጮች ላይ በቀጥታም ሆነ በስውር እየደረሰ ያለው ዘግናኝ የሆነ የስነ ልቦና፣ የእስራት፣ የግድያና የአፈና እርምጃ የስርዓቱን አረሜንነት መገለጫዎች ናቸው ብለን እናምናለን።

ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ግን ገዢው ፓርቲው ኢሕአዴግ ኢ ሰብኣዊ ድርጊቱንና ተፈጥሮውን ለመሸፋፈን አሁኑም ነፃ ምርጫ እንዳለ ለማስመሰል ይሞክር እንጂ ምርጫ ነፃ የፍትሕና የዲሞክራሲ ተቋማት በሌሉበት፣ የብዙሃን መገናኛ አውታሮች በአንድ ፓርቲ ሞኖፓል በተያዙበት፣ የሕገ የበላይነት ባልተረጋገጠበት፣ የዜጎች የሕግና የሕገ መንግስት ዋስትና አደጋ ላይ ወድቆ ሽብር፣ ፍርሃትና ግድያ በነገሰበት፣ ብቃት ያለው ገለልተኛ የምርጫ ኮሚሽን በሌለበት፣ ነፃ የህዝብ ተሳትፎ በሌለበት፣ ሕግ የሚገዛው መንግስትና በሕግ የሚስተዳደር ሕብረተሰብ በሌለበት፣ ህዝብና መንግስት ሆድና ጀርባ በሆኑበት፣ በአጠቃላይ የፓለቲካ ምሕዳሩ በአንድ ድርጅታዊ ሞኖፓል እጅ ወድቆ ገዢ ፓርቲው ራሱ ከሳሻ፣ ራሱ ዳኛ፣ ራሱ መስካሪ፣ ራሱ አሳሪ፣ ራሱ ገዳይ ራሱ አጣሪ በሆነበት አስፈሪ ሁኔታ ላይ ሆኖ ሚዛናዊ፣ ፍትሃዊ፣ ተኣሚኒና ርትዓዊ ምርጫ ይካሄዳል ብሎ ማሰብ ከእባብ እንቁላል ርግብ ይወለዳል ብሎ እንደ መጠበቅ ያህል መሆኑን እንገነዘባለን።

## የተከበራችሁ ውድ ኢትዮጵያውያን ሆይ !!

እየገደሉና ኩሮጆ እየገለበጡ ስልጣን በምርጫ ሳይሆን በአቋራጭ በጡንቻ መንጠቅ የለመዱ የህወሓት መሪዎች የህዝብ ትግል እያየለ በሄደ ቁጥር እየተደናገጡ ዛሬም ካለፈው ሳይማሩ ስድብ፣ ማስፈራራት፣ ግድያና አፈና እንደ ልዩ ሞያና ችሎታ አድርገው በመውሰድ በልቡ የሸፈተ ህዝብ ይዘው ዘላለማዊ ስልጣን እናረጋግጣለን ብለው የእብሪት ስራ ሲሰሩ ስናይ በንፁኃን ደም የሰከሩና በስልጣን ጥማት ዓይናቸው የታወሩ መሪዎች መውደቂያቸው ሲቃረብ ምን እንደሚሉና ምን እንደሚያደርጉ መገንዘቡ ብዙም አያዳግትም።

ለምሳሌ የትግራይ ህዝብ መፈናፈኛ በማሳጣት በጁሆ (ሆስቴጅ) ይዞ በሞኖፓል በመግዛት ላይ ያለው አምባ ገነን መሪ መለስ ዜናዊ ባለፈው ሳምንት የህወሓት 35ኛው የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ በመቀሌ ከተማ ተገኝቶ ያስተላለፈው መረኑ የለቀቀና መርዝ የተላበሰ ንግግር ስንመለከት እጅግ አሳዛኝና አሳፋሪ ነው። ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ነገር ለዲሞክራሲ ብለው የተሰዉ ታጋዮች ክብርና እንዲሁም የትግራይ ህዝብ ጨዋነት የሚያራክስ የፍርሃትና የጭንቀት ንግግር ሆኖ አግኝተኗል። የንግግሩ እንድምታም ቀደም ሲል ለ17 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን አንቀጥቅጠው የገዙት ኰለኔል መንግስት ሓይለማሪያም ስልጣን በያዙበት ማግስት ጠላቴና ፀረ አብዮት ለሚሉዋቸው ሰዎች ለመምታት ሲሉ በአዲስ አበባ በመስቀል አደባባይ ላይ ቆሞው ደም የተሞላ ጠርሙስ በተሰበሰበው ህዝብ ፊት ወደ መሬት የወረወሩበትን ቀንና እሱን ተከትሎ የመጣዉን መዘዝ ያስታውሰናል።

አረሜኔው መለስ ዜናዊ የህዝቡን ትእግስትና ጨዋነት እንደ ፍርሃትና ሞኝነት በመቁጠር ዛሬም ህዝቡ እርሱ በርሱ ለማጨፋጨፍና ለማተራመስ በመቀሌ ከተማ ለትግራይ ህዝብ ብሎ ያስተላለፈው የጥፋት አዋጅ ተከትሎ ሳይውል ሳያድር በመላ ሀገሪቱ በተለይም ላለፉት በርካታ ዓመታት የጥፋት አውድማና መረማመጃ ሆኖ በጦርነት በደቀቀዉ በትግራይ ህዝብ ላይ ዳግም የመንጥር ዘመቻ በማፋፋም እኖሆ በገዛ ሃገራቸው እንደ ጠላት ተቆጥረው እንደ በግ የታረዱ፣ የተደበደቡና ከስራ የተባረሩ ዜጎች መርዶ ስንሰማ እጅጉን አሳዝኖናል። አስቆጥቶናልም። በዚህ ጉዳይ ላይ ያለን ስጋት ምርጫውን ማን ያሸንፋል ሳይሆን ህወሓት/ኢሕአዴግ በተለይም መሪዎቹ ሀገሪትዋን ወደ ባሰ ትርምስና እልቂት ለማስገባት እየተከተሉት ያሉት አውዳሚ ፓሊሲና በየአደባባዩ የሚያሰሙት የተሳሳተ ዲስኩር ተከትሉ በዜጎቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ግድያና አፈና የሚያመጣው ጉዳትና መዘዙ ከባድ መሆኑን ስለምንረዳ ነው። ስለሆነም ድርጊቱን በማዉገዝ የሚከተሉትን የጋራ የአቋም ነጥቦች እናቀርባለን።

1. በራሱና በህዝቡ የማይተማመን አምባ ገነኑ መለስ ዜናዊ ሕግ፣ ባህል፣ ታሪክና ወግ ባልገዛው አንደበቱ ሕጋዊ ፍቃድ አግኝተው፣ ገዢው ፓርቲ ያወጣውን ሕግና ደንብ ተቀብለው፣ ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል አምነው፣ በሕገ መንግስቱ ጥላ ስር ሆነው በሰላም የሚታገሉ ሰዎች ለሀገርና ለወገን ይጠቅማል የሚሉትን የተለየ አመለካከት ስለያዙ ብቻ እንደ ጠላት በመቁጠር በወገኖቻችን ላይ የደረሰው ግድያ፣ ድብደባና ወከባ አጥብቀን እናወግዛለን።
2. አምባ ገነኑ መለስ ዜናዊ ለዘመናት አብሮ በፍቅርና በመተባበር የሚኖረው ህዝብ "አንተ ወዳጅ አንተ ጠላት" እያለ በመከፋፈል ዕድሜ ልኩን እሳት እየለኰሰ ወንድማማች ህዝቦችን ሲያፋጅና ሲያናቁር ኖሯል። ለራሱ ከሕግ በላይ ሆኖ ለሕግ የበላይነት የቆሙ እንደነ ብርቱኳን ሜዴክሳ የመሳሰሉትን ዜጎች አፍ እላፊ ብሎ ዕድሜ ልክ ወህኒ ቤት አስገብቷል። ሌሎች ዜጎች ደግሞ ሽብርተኞች ናችሁ እያለ ሲያንገላታ ቆይቷል። ነገር

ግን ራሱ መለስ ዜናዊ ትናንት የፈረመበት የስነ ምግባር ደንብ ቀለም ሳይደርቅ ሕግ አክብረው ለሚንቀሳቀሱ ዜጎች ከመሬት ተነስቶ "ገለባ፣ ርጋፊ፣ ጭቃ፣ እንክርዳድ፣ ጠላት" ብሎ መናገሩ ብቻ ሳይሆን በዚሁ ሰበብ ሂይወት ጠፍቷል። ሕገ መንግስቱን ተዳፍሯል። ስልጣኑን መከታ በማድረግ ጠላት መጣብህ እያለ ህዝብ ከህዝብ ለማጋጨት አሸባሪ ድርጊት ፈፅሟል። ሕገ መንግስቱን በመጣስ የዜጎች ሰብአዊ ክብርና ዲሞክራሲያዊ መብት ተዳፍረዋል። በመሆኑም በሕገ ደንቡ መሰረት በሀገሪቱ ለሁሉም ዜጎች እኩል የሚዳኝ የሕግ የበላይነት ካለ ይህ አሸባሪና አረሜኔ መሪ በሕግ እንዲጠየቅ የሚመለከታቸው የዳኝነትና የፍትሕ አካላት ሁሉ ጧሪ በሌላቸውና አባት አልባ ሆነው በቀሩ ህፃናት ስም እንማፀናለን።

3. የሰማንያ ሚሊዮኑን ህዝብ ዕድልና መብት ወሳኝ የሆነውን የምርጫ ስርዓት የሚከታተል የምርጫ ኮሚሽን የውድድሩ መድረክና የውድድሩ መጫወቻ ሜዳ የጥቂት አምባ ገነን መሪዎች መፈንጫና የትርምስ አውድማ ሳይሆን በሀገሬ ጉዳይ ላይ ያገባኛል የሚለውን ተወዳዳሪ ሓይል ሁሉ ያለ አድልዎና ማስፈራሪያ ከአፈ ሙዝ ነፃ ሆኖ ለተመራጩም፣ ለመራጩም፣ ለአስመራጩም፣ ለታዛቢውም አመቺነት ያለው እንዲሆን አበክረን እናሳስባለን። የህወሓት መሪዎች እንደሚሉት ውድድሩ በጠላትና በወዳጅ መካከል ሳይሆን እኩል መብትና ዜግነት ባላቸው ሓይሎች መካከል የሚካሄድ ምርጫ እንዲሆን እንጠይቃለን።

4. በትግራይ የህወሓት መሪዎች ያለ ተወዳዳሪ ተመርጠናል ብለው በበራሪ ወረቀት የሚሸኑበት ሁኔታ እንደነበር የሚታወስ ነው። ዛሬ ግን ሁኔታው ተቀይሮ ከህዝቡ አብራክ የወጡ ሌሎች እንደነ መድረክ የመሳሰሉ ብቅ ስላሉ በህወሓት/ኢሕአዴግ መንደር ትልቅ ፍርሃትና መደናገጥ ፈጥሯል። በመሆኑም የገበያ ግርግር ለሌባ ይመቻል እንዲሉ የህወሓት መሪዎች ውድድር የሚለውን ቃል ያልለመዱት ነገር ስለመጣባቸው እንደጀመሩት የውድድሩ መድረክ ለማደፍረስና መስመሩ ለማሳሳት በስውርም ሆነ በጋሃድ ጥረት ማድረጋቸው የማይቀር ነው'። ስለሆነም ህዝቡ ሳይደናገጥ በሰለጠነና በሰከነ መንፈስ የመመረጥና የመምረጥ መብቱ ማስከበር ይኖርበታል እንላለን። እኛም የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫው ፍትሓዊና ሚዛናዊ እንዲሆን በምታደርገው የጋራ እንቅስቃሴ እስከ መጨረሻ ከጎንህ እንደምንሰለፍ እናረጋግጣለን።

5. በሀገር ውስጥና በመላ ዓለም የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ አምባ ገነናዊው ስርዓት እኛን ሆድና ጀርባ አድርጎ ለያይቶ በየተራ እየረገጠ ሲገዛንና ሲያደማን እንዳይኖር መብታችን፣ ህልውናችንና ነፃነታችንን ለማስከበር የምንተባበርበትና አንድነታችንን የምናድስበት ጊዜው አሁን ነው እንላለን።

6. በዚሁ አጋጣሚም አቶ አረጋዊ ገብረ ዮሐንስ በተወለዱባት ምድር በጉልበተኞች በግፍ እንደ በግ ታርደው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው የተሰማንን ሃዘን እንገልፃለን። እንዲሁም ለቤተሰቦቻቸውና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው በሙሉ መፅናናትን እንመኛለን።

የአንድ ታጋይ ሞት ሽዎች ታጋዮች እንደሚያፈራም አንጠራጠርም።